# ኢትዮጵያዬ

ሀሴትን አገኛለሁ በአንቺም ይለኛል ደስ፣
ድምጽሽ እንደዝማሬ ከሰማየ ሰማያት ሲፈስ።
እንደ የንጋት ብሥራት የአእዋፋትም ውዳሴ፣
በስምሽ እከብራለሁ ደስም ይሰኛል ነብሴ።
የት ወዴት ብዬ እማልጠይቅ በሄድሽበት የምነጉድ፣
እንደ ሎሌሽ ጋሻ ጃግሬሽ ከመጫሚያሽ የምሰግድ።
ከቶም የማይሰጠኝ ግድ ብታዝዢበት በህይወቴ፣
ይህ መረታቴ ምንኛ ነው እስቲ ንገሪኝ በሞቴ።
በሳቅሽ እንድማልል በደስታሽ እንድቦርቅ፣
በቁጣሽ እንድፈራ በኩርፊያሽ እንድሳቀቅ፤
በራሴው ምርጫ የምሸነፍ ሽንፈቴም የሚያኮራኝ፣
በምን ጥበብሽ ታሰርኩ ለምንስ ያንቺ አረገኝ?

ገና ስርቅሽ ባዶ እምሆን አንዳች የሌለው ነገር፣
ሳቅ ደስታዬን የምነጠቅ አንደበቴ እሚተሳሰር፤
አብሬሽ እያለሁ ከጉያሽ ልብ ያላልኩትን ሁሉ፣
ስርቅሽ የምናፍቀው ግራ ግብት የሚለኝ ውሉ፤
ልቤን የሚያሞቅ መዓዛሽ ከከርቤ ከሽቶ የሚልቅ፣
ምንኛ ጥምረት ነው ህልውናዬ በአንቺ የሚደምቅ?
ብርር የሚለው አሳቤ ወደ አንቺ የሚያከንፈኝ፣
እንዴት ያለስ ፍቅር ነው ከአንቺ ጋር ያቆራኘኝ?
በሳቅሽ እንድማልል በደስታሽ እንድቦርቅ፣
በቁጣሽ እንድፈራ በኩርፊያሽ እንድሳቀቅ፤
በራሴው ምርጫ የምሸነፍ ሽንፈቴም የሚያኮራኝ፣
በምን ጥበብሽ ታሰርኩ ለምንስ ያንቺ አረገኝ?

ሬቱ የኑሮ ገፈት እለት በእለት ቢያሯሩጠኝ፣
ልቤ ያንቺ ነውና በኔ ተስፋ አትቁረጪብኝ።
ምሬት አንገሸግሾኝ በንዋይ ፍቅር ታብዬ፣
በአንቺ ልቤ አይሸፍትም እናቴ ነሽ እምዬ።
በደስታሽ እምፈነጥዝ በሀዘንሽ አጥንቴ እሚሰበር፣
ማጣትሽ እንኳ ቢያይል የአንቺ ነኝ ስል የማላፍር።
የመንከራተቴ ምሬት ሀሳቤን ከአንቺ የማይነጥል፣
የዘመን ብዛት የማይሽረው ላይፈታ የታሰረ ውል፤
ምን አይነት ቁርኝት ነው? እንዴትስ ያለ የትንቢት ቃል?
በሳቅሽ እንድማልል በደስታሽ እንድቦርቅ፣
በቁጣሽ እንድፈራ በኩርፊያሽ እንድሳቀቅ፤
በራሴው ምርጫ የምሸነፍ ሽንፈቴም የሚያኮራኝ፣
በምን ጥበብሽ ታሰርኩ እንደምንስ ያንቺ አረገኝ?

ለንጹህ ያገር ፍቅር፣ ለውብ ሕዝብዋም ክብር ተጻፈ
ከትንሣዔ
ሐምሌ ፳፱